## የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን

## የምርት ገበያ የክፍያና ርክክብ ዋስትና ፈንድ መመሪያቁጥር 540/2013

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን የምርት ገበያው ስራዉን በአግባቡ ማከናወኑን ለመቆጣጠር በህግ የተቋቋመ በመሆኑ

የምርት ገበያው ተግባሩን በሚገባ እንዲያከናዉን የአደጋ አስተዳደር ሥርዓት ሊዘጋ እንደሚገባው በማመኑ የምርት ገበያ ክፍያና ርክክብ ዋስትና ፈንድ ማቋቋምና የፈንዱን አሰባሰብ፣ አጠባበቅ፣ አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 አንቀጽ 31 እና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 550/1999 አንቀጽ 27 መሠረት የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ የምርት ገበያ የክፍያና ርክክብ ዋስትና ፈንድ መመሪያ ቁጥር 540/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር

   1) **ባለስልጣን** ማለት በአዋጅ ቁጥር 551/1999 መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ገበያ ባለስልጣን ማለት ነው፡፡
   2) **ግዴታውን ያልተወጣ አባል** ማለት በምርት ገበያው ደንብ መሠረት ለፈጸመው ግብይት የገባውን የክፍያና የርክክብ ግዴታ ለመውጣት ያልቻለ የምርት ገበያው አባል ማለት ነው፡፡
   3) **አገናኝ አባል** ማለት ለራሱም ሆነ ለደንበኞቹ ማበያየት የሚችልና ለፈጸመው ግብይት ክፍያና ርክክብ የመውጣት ኃላፊነት ያለበት የምርት ገበያው አባል ማለት ነው፡፡
   4) **ፈንድ** ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት የሚቋቋምና የሚተዳደር የክፍያና ርክክብ ዋስትና ማለት ነው፡፡
   5) **የምርት ገበያ** ማለት በአዋጅ ቁጥር 550/1999 መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በባለስልጣኑ እውቅና ያገኘ ሌላ ምርት ገበያ ማለት ነው፡፡
   6) **ተገበያይ አባል** ማለት ለራሱ ብቻ ማበያየት የሚችልና ግዴታውን የመወጣት ኃላፊነት ያለበት የምርት ገበያው አባል ማለት ነው፡፡
   7) **ወሰን አገናኝ አባል** ማለት በምርት ገበያው አንድ ምርት ብቻ ለራሱም ሆነ ለደንበኞቹ ማሻጥና ክፍያና ርክክብ ሚፈጸም የሚችል የምርት ገበያው አባል ማለት ነው፡፡

8) **ክፍያ ፈጻሚ ገዢ ብቻ ተገበያይ አባል** ማለት በምርት ገበያው አንድ ምርት ብቻ ለራሱ መግዛትና ክፍያና ርክክብ ሚጸም የሚቻል የምርት ገበያው አባል ማለት ነው፡፡
9) **ክፍያ የሚፈጽም ገዢ ወይም ሻጭ ብቻ ተገበያይ አባል** ማለት በምርት ገበያው አንድ ምርት ብቻ ለራሱ መሸጥ ወይም መግዛት የሚቻል ነገር ግን ክፍያና ርክክብ ሚጸም የሚችል የምርት ገበያው አባል ማለት ነው፡፡
10) በዚህ መመሪያ ወስጥ በወንድ ጾታ የተገለፀው ሴትን ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ፈንዱ መቋቋምና መዋጮ

### 3. ስለ ፈንዱ መቋቋም

1) የምርት ገበያው በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰባሰብ፣ የሚተዳደርና ጥቅም ላይ የሚውል የምርት ገበያ ክፍያና ርክክብ ዋስትና ፈንድ ያቋቁማል፡፡
2) እያንዳንዱ የምርት ገበያው አባል ቢያንስ ዝቅተኛውን የመዋጮ መጠን ለፈነዱ ማዋጣት አለበት፡፡
3) ፈንዱ በምርት ገበያው የሚተዳደር ይሆናል፡፡
4) ምርት ገበያው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በየጊዜው የክፍያና የርክክብ የኢንሹራንስ ስርዓት ሊያመቻች ይችላል፡፡

### 4. ለፈንዱ ስለሚደረግ መዋጮ

1) ማንኛውም አገናኝ አባል ለአባልነት መደቡ ከሚፈለገው ዝቅተኛው የተጣራ ሀብት ቢያንስ 30 በመቶውን ለፈንዱ ማዋጣት አለበት፡፡
2) ማንኛውም ተገበያይ አባል ለአባልነት መደቡ ከሚፈልገው ዝቅተኛው የተጣራ ሀብት ቢያንስ 40 በመቶውን ለፈንዱ ማዋጣት አለበት፡፡
3) ማንኛውም ወስን አገናኝ አባል ቢያንስ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ለፈንዱ ማዋጣት አለበት፡፡
4) ማንኛውም ክፍያ ፈጻሚ ገዢ ብቻ ወስን ተገበያይ አባል ቢያንስ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ) ለፈንዱ ማዋጣት አለበት፡፡
5) ማንኛውም ክፍያ የሚፈጽም ገዢ ወይም ሻጭ ብቻ ተገበያይ አባል ቢያንስ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) ለፈንዱ ማዋጣት አለበት፡፡
6) አባሉ ለፈንዱ ያዋጣው መዋጮ በማናቸውም ምክንያት ከሚፈልገው ዝቅተኛ መጠን በታች ከሆነ ጉድለቱ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በሁለት ሣምንታት ጊዜ ወስጥ ማሟላት አለበት፡፡
7) ምርት ገበያው ለፈንዱ መዋጮ ማዋጣት ይችላል፡፡
8) መንግስት ወይም ሌላ ሶስተኛ ወገን ለፈንዱ መዋጫ ማዋጣት ወይም በምርት ገበያው እንዲገባያዩ ለተፈቀደላቸው ተለይተው ለታወቁ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች ዋስትና ማስጠት ይችላል፡፡

**5. ለፈንዱ የሚደረገዉ መዋጮ ማጠን ስለማካለስ**

1) ለፈንዱ አስፈላጊ በሆነ ማጠን የምርት ገበያው፣ የአባሉን የግብይት ማጠን በእንጥልጥል ላይ ያሉ የክፍያና ርክክብ ግዴታዎችን ዋጋ፣ እና ግብይት የሚደረግላቸዉን የደንበኞች ብዛትና የገበያ ሁኔታዎችን ከግምት ወስጥ በማስገባት ምርት ገበያው በየዓመቱ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከዚህ ባነሰ ጊዜ ለየአባልነት ሟደቡ የሚያስፈልገዉን መዋጮ በማካለስ ማስተካከል ይችላል፡፡
2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተደረገው ክለሣ በባለሥልጣኑ ሲጸድቅ ምርት ገበያው አባሉ ተጨማሪዉን መዋጮ እንዲያዋጣ ያደርጋል፡፡
3) ምርት ገበያው በዚህ አንቀፅ በተደረገው ክለሣ መሠረት የሚፈለገዉን ተጨማሪ መዋጮ ለአባላት ማሣወቅ አለበት፡፡
4) አባሉ በተደረገው ክለሣ መሠረት ተጨማሪ መዋጮ ተጠይቆ ሣያዋጣ የቀረ እንደሆነ ምርት ገበያው በጉድለት በታየው ገንዘብ ልክ አስቀድሞ የተወሠነዉን ወለድ ለማጠየቅና አስፈላጊዉን የዲስፒሊን እርምጃ ለመዉሠድ ይችላል፡፡
5) ለየአባልነት ሟደቡ የሚያስፈልገው መዋጮ ላይ በተደረገው ማስተካከያ መሠረት አባሉ ቀደም ሲል ያዋጣው በልጦ ከተገኘ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 6 የተመለከተዉን ከግምት ወስጥ በማስገባት ምርት ገበያው፡ –

   ሀ) የተረፈዉን ወይም ቀሪዉን በዋስትና ሜልክ የተሰጠ መዋጮ እና

   ለ) የተረፈዉን ወይም ቀሪዉን በጥሬ ገንዘብ ሜልክ የተሰጠን መዋጮ መመለስ ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት
## ለፈንዱ የሚደረገው መዋጮ ዓይነት እና ስሌቱ

**6. የመዋጮ አይነት**

1) ሁሉም ተገበያይና አገናኝ አባላት ለፈንዱ የሚያዋጡት መዋጮ በጥሬ ገንዘብ መሆን አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ምርት ገበያው እስከ 10 በመቶ የሚሆነዉን መዋጮ በመንግስት ቦንድ ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት ቦንድ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እስከ 40 በመቶ የሚደርሰዉን በኢንሹራንስ ወይም የባንክ ክፍያ አፈጻጸም ዋስትና እንዲዋጣ ሚድረግ ይችላል፡፡

**7. በዋስትና ሜልክ የሚሰጥ መዋጮ እና ከመዋጮ የሚገኝ ገቢ**

1) ምርት ገበያው በዋስትና ሜልክ የተሰጡ መዋጮዎችን ስሌት የገጽ ዋጋቸዉንና ሊፈጡሩ የሚችሉ ከሰራዎችን ምጣኔ ከግምት ወስጥ በማስጋበት ሊወስን ይችላል፡፡
2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 2 መሠረት አባሉ በዋስትና ሜልክ ካዋጣው መዋጮ የሚገኝ ወለድና ገቢ ማኑ ባለመበት ነው፡፡

## ክፍል አራት
## የፈንዱ አቀማመጥና አጠባበቅ

**8. የፈንድ አቀማመጥ**

1) በጥሬ ገንዘብ ሜልክ የሚደረግ የፈንዱ መዋጮ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በተመለከተው መሠረት በምርት ገበያው ስም በተከፈተ ባንክ ተቀማጭ ሂሳብ ወይም የግምጃቤት ሰነድ ሊቀመጥ ይችላል፡፡
2) ምርት ገበያው በዋስትና ሜልክ ለተሰጡ መዋጮዎች አስተማማኝ ጠበቂዎችን ሊሰይምይችላል፡፡ እነዚህ ጠበቂዎች ፈንዱን ወጪ ቆጣቢ በሆነ አሠራርና በታማኝነት ለማስተዳደር ባላቸው ብቃት መሠረት የሚሟጡ ይሆናል፡፡

## 9. ለሚደርስ ጉዳት ሃላፊነት ስለመውሰድ

1) ምርት ገበያው ስለ ፈንዱ አጠባበቅና ደህንነት ሀላፊ ይሆናል፡፡
2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 ከተመለከተው ወጪ ፈንዱ በሙሉም ሆነ በከፊል ቢጎድል ወይም ቢጠፋ ምርት ገበያው ወዲያው መተካት አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## በፈንዱ ስለሚደረግ ኢንቨስትምንትና ከኢንቨስትመንቱ ስለሚገኝ ገቢ ባለቤትነት

## 10. የተፈቀደ ኢንቨስትመንት

1) ምርት ገበያው ፈንዱን ወለድ በሚያስገኝ የባንክ ተቀማጭ ሊያስቀምጠው ወይም ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ አማራጮች ሊያወለው ይችላል፡፡
   ሀ) የምርት ገበያው በጥሬ ገንዘብ ሜልክ የያዘውን ፈንድ ተከፋይ ግዴታዎችን፣ ከአማራጮቹ ሊገኝ የሚችለውን ገቢና ኪሳራዎች ከግምት ወስጥ በማስገባት በሚወሰን ምጣኔ ለግብጃ ቤት ሰነድ ወይም ወለድ የሚያስገኝ የባንክ ተቀማጭ
   ለ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ሀ) ለተጠቀሰው ዓላማ ምርት ገበያው ባንኮችን ወይም አስቀሚጮችን የሚሟርጠው በግልፅ ጨረታ ተወዳድረው በሚቀርቡት ከፍተኛ የወለድ ማጠን መሆን አለበት፡፡
2) ምርት ገበያው በአንድ ባንክ የሚያስቀምጠው ጠቅላላ ማጠን ፈንዱ ካለው የጥሬ ገንዘብ ተቀማጭ 50% መብለጥ የለበትም፡፡

## 11. የኢንቨስትመንት ገቢ ባለቤትነት

1) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከፈንዱ ኢንቨስትመንት የሚገኝ ወለድ እና ገቢ የፈንዱ አካል ይሆናል፡፡
2) የምርት ገበያው አባላት ለፈንዱ በጥሬ ገንዘብ ካደረጉት መዋጮ ከሚገኝ ወለድና የኢንቨስትመንት ገቢ ላይ የባለቤትነት መብት የላቸውም፡፡

## ክፍል ስድስት

## ፈንዱ ጥቅም ላይ ስለሚውልበት፣ ስለሚተካበትና ተመላሽ ስለሚሆንበት ሁኔታ

**12. ስለ ፈንዱ አጠቃቀም**

1) ምርት ገበያው በዚህ መመሪያና በደንቡ በተደነገገው መሠረት ፈንዱን ጥቅም ላይ ለማዋል ሙሉ ሥልጣን አለው፡፡ ይህም የሚከተሉትን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

   ሀ) ፈንዱን ለማቋቋምና ለማስተዳደር ለሚውሉ ወጪዎች፣

   ለ) የምርት ገበያው ክፍያና ርክክብ ፈጻሚ አባላት በምርት ገበያው ህጎች መሠረት የተፈጸሙ ግብይት ግዴታ ባለመወጣታቸው የተነሳ ለሚቀርቡ ጊዜያዊ ጉድለቶች፣

   ሐ) ከክፍያና ርክክብ ጋር በተያያዘ ምርት ገበያው ለሚያጋጥሙት አደጋዎች ለተገባ ኢንሹራንስ አረቦን ክፍያ፣

   መ) ከክፍያና ርክክብ ጋር በተያያዘ ምርት ገበያው ለሚያጋጥሙት ኪሳራዎችና እዳዎች ክፍያ፣

   ሠ) የምርት ገበያው አባል አባልነቱን ሲያቋርጥ በምርት ገበያው ደንብ መሠረት ያለበትን እዳ ሁሉ ከከፈለ በኋል ቀሪውን ለአባሉ ለመመለስ፣

   ረ) አገናኝ አባሉ የደንበኛውን ክፍያ ለደንበኛው አለማስተላለፉ ወይም አለመክፈሉ ሲረጋገጥ ለደንበኛው ክፍያ ለሚፈፀም፣

   ሰ) በምርት ገበያው አቅራቢነት ባለስልጣኑ ለሚያፀድቃቸው ሌሎች አላማዎች፣

2) አንድ አባል ከግብይት የሚመነጩ ለምርት ገበያው የሚፈፀሙ ክፍያዎችንና ርክክቦችን መወጣት ሲያቅተው ወይም አንድ አባል ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑ ሲገለፅ የምርት ገበያው የአባሉን የክፍያና ርክክብ ሚፈፀሚያ ዋስትና ፈንድና ሌሎች ገንዘቦች እንዳስፈላጊነቱ ግዴታውን ለማሟላት በሚከተለው ቅደምተከተል መሠረት ማጠቀም ይቻላል፡ –

   ሀ) ግዴታውን ያልተወጣው አባል የከፈለው ማንኛውም የቅድመ ግብይት ተቀማጭ /የደንበኛ ቅድመ ግብይት ተቀማጭን ሳይጨምር/ የክፍያና ርክክብ ግዴታን ለመወጣት የተቀማጠ ወይም በምርት ገበያው የተያዘ ገንዘብ፣

   ለ) ግዴታውን ባልተወጣው አባል እንደተጨዌ ተቀማጭ በምርት ገበያው ዘንድ የተቀማጠ ማናቸውም ገንዘብ፣

   ሐ) በምርት ገበያው ባለቤትነት የተያዘን የአባልነት መብት በማሻጥ የሚገኝ ትርፍ ካለ እንደአስፈለጊነቱ ከሐራጁ ወይም ከሽያጩ ጋር የተያያዙ ወጪዎችን በመቀነስ፣

   መ) በምርት ገበያው በሚወሰነው መሠረት ከቅጣት ክፍያዎች፣ የክፍያና ርክክብ ሚፈፀሚያ ዋስትና ፈንዱን ኢንቨስት በሚደረግ ከሚገኝ ትርፍ ወለድ ወይም ሌላ ገቢ፣

   ሠ) በክፍያና ርክክብ ሚፈፀሚያ ዋስትና ፈንዱ ወስጥ ባላቸው ተቀማጭ ማጠን ሁሉም አባላት ያስቀማጡት ማጠበቂያ። የምርት ገበያው አስፈላጊ ነው ብሎ በሚያምነው ጊዜ ወስጥ አባላት የጉደለውን ማጠን በክፍያና ርክክብ ሚፈፀሚያ ዋስትና ፈንዱ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል።

   ረ) በምርት ገበያው፣ በመንግስትና በሌላ ሦስተኛ ወገን ለክፍያና ርክክብ ሚፈፀሚያ ፈንዱ የተደረጉ መዋጮዎች፣ ካሉ።

3) በቅድሚያ በባለስልጣኑ ሜፀደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ምርት ገበያው ከጊዜ ወደ ጊዜ በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን ፈንዱ ጥቅም ላይ የሚውልበትን አግባብና ቅደም ተከተል ማለወጥና ማስተካከል ይችላል፡፡

**13. ከፈንዱ ወጪ የሆነን ማጠን ሜሰ ስለመተካት**

1) ምርት ገበያው በአንቀጽ 12 ለተዘረዘሩት ማቻቻያዎች ከዋስትና ፈንዱ የተከፈለ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ሲተካ ይህንኑ ገንዘብ ወደያውኑ ወደ ፈንዱ ተመሌሶ እንዲገባ ያደርጋል፡፡
2) ከአባሉ መዋጮ ላይ ተቀንሶ ለግዴታ ማሟያ የዋለ ከሆነና አባሉ ገንዘቡን የተካ ከሆነ የተመሇሰው ገንዘብ በዚህ መመሪያና በምርት ገበያው ደንብ በተደነገገው መሠረት በአባሉ ስም መመዝገብና አባሉ ያዋጣው ማጠን ላይ መደመር ይኖርበታል፡፡
3) ግደታወን ያልተወጣው አባል መዋጮ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 መሠረት የወጣወን ወጪ ሙሉ በሙሉ የሚሸፍን ከሆነ አባሉ ለአባልነት መደቡ የሚፈለገወን መዋጮ በትርፍ ለደረሰው ጉዳት የተከፈለወን ገንዘብ ማጠን በሙሉ መተካት አለበት፡፡

**14. የአባል መዋጮ ስለመመለስ**

1) አባልነት ሲቋረጥ ምርት ገበያው የአባሉ እዳዎች በሙሉ መከፈላቸውን ካረጋገጠ በኋላ በጥሬ ገንዘብና በዋስትና ሜልክ ያለወን ቀሪ መዋጮ በ3 ወር ጊዜ ወስጥ ለአባሉ መመለስ አለበት፡፡
2) አባልነት በሚቋረጥበት ጊዜ የአባሉ መወጮ በምርት ገበያው ያሉበትን እዳዎች ሙሉ በሙሉ የሚሸፍን ከሆነ አባልነቱን ለሚቋረጥ ቀሪ እዳወን መከፈል ይኖርበታል፡፡

**<u>ክፍል ሰባት</u>**

**<u>ፈንዱን ስለማስተዳደር፣ ስለአስተዳደር ወጪዎችና ሚዲያዎች</u>**

**15. ፈንዱን የሚያስተዳድር የስራ ክፍል ስለሚደራጀት፣**

1) ምርት ገበያው ፈንዱን በዚህ መመሪያና በምርት ገበያው ደንብ መሠረት የሚተዳደርና የሚመራ የስራ ክፍል ያደራጃል፡፡
2) የምርት ገበያው የስራ ክፍሉን ዝርዝር ተግባራት ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

**16. የፈንዱ አስተዳደራዊ ወጪዎች**

1) ፈንዱን ለማቋቋም፣ ለማጠበቅ፣ ለማምራትና ለማስተዳደር የሚወጣ ወጪ ከፈንዱ፣ ከወለደና ፈንዱን ኢንቨስት በማድረግ ከሚገኝ ገቢ የሚከፈል ይሆናል፡፡
2) አስተዳደራዊ ወጪው በፈንዱና ከፈንዱ ከሚገኝ ገቢ የሚሸፈን ከሆነ የምርት ገበያው ጉድለቱን አባላት በማራት እንዲተኩት ሊያደርግ ይችላል፡፡
3) ባለስልጣኑን በቅድሚያ በማስፈቀድ የምርት ገበያው ፈንዱን የሚያስተዳድርና የሚመራ ሌላ ተቋም ለሰይም ይችላል፡፡

**17. ፈንዱን የተመለከተ ሚዲያ**

ምርት ገበያው፡ –

1) በእያንዳንዱ አባል በማለየት ከሚኣሻ የተዋጣውን፣ በተጨማሪ የተዋጣውን፣ ክፍያዎች ወይም ተቀናሾችን እና ቀሪውን በተለየ ማዝገብ ማያዝና በየጊዜው ለአባላት ማሳወቅ አለበት፣
2) የእያንዳንዱን አባልና የፈንዱን ጠቅላላ እንቅስቃሴ፣ ኢንቨስትመንት፣ ክፍያ፣ ገቢ፣ ወጪና ሌሎች ተዛማጅ ሚጃዎችን ከምርት ገበያው ሌሎች የፋይናስ ገቢና ወጪ እንቅስቃሴዎች ለይቶ ማያዝ አለበት፡፡
3) የተዋጣውንና ጥቅም ላይ የዋለውን መዋጮ በየጊዜው የተደረገውን ክለሣና ይህንኑ ተከትሎ የተደረጉ ለውጦችን ወጪዎችንና ለአባላት ተመላሽ የተደረጉ መዋጮዎችን በተመለከተ ለባለስልጣኑ በየወሩ የመጀመሪያ ሣምንት ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡
4) በየዓመቱ ፈንዱን ኦዲት በማስደረግ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 18. ስለ ቅጣት

ምርት ገበያው ወይም ማንኛውም የምርት ገበያ አባል ወይም ሰራተኛ ይህንን መመሪያ የጣሠ መሆኑ ከተረጋገጠ ባለስልጣኑ አስተዳደራዊና የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል፡፡

### 19. ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ህጎች

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ የወስጥ ደንብ ወይም አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### 20. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ቦርድ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ጥር 16 ቀን 2003 ዓ/ም

አዲስ አበባ